# ዋዜማ

## በማግስቱ የኢትዮጵያ ነገስታት
## የታሪክ በዓል ለማክበር

### ተጻፈ

### ከኅሩይ ወልደ ሥላሴ

በ1921 ዓመተ ምሕረት በጎሕ ጽባሕ ማተምያ ታተመ

### አቃቂር

### ከ ዶ/ር ገላውዴዎስ አርኣያ

January 5, 2009

ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ መጽሓፉን ደርሰው ለሕተመት ያበቁት በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1921 ዓ.ም. ነው። ይኸንን መጽሓፍ ከመድረሳቸው አስራ አንድ ዓመት በፊት ማለትም በ1910 ደግሞ 'ለልጅ ምክር ላባት መታሰብያ' በሚል ርእስ የጻፉትን አነስተኛና ቁም-ነገር አዘል መጽሓፍ ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሜዋለሁ። ክብርም ይሰማኛል።

የ 'ዋዜማ' አቃቂር እጥር ምጥን ብሎ የመጽሓፉ ይዘትና መልእክት ለአንባቢ ለማቅረብ የተደረገ ጥረት እንጂ በሰፊውና በጥልቀት ትችት ለማቅረብ አይደለም። መጽሓፉ በመጀመርያው እትም ላይ፣ ደራሲው "ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ በመስከረም 27 ቀን 1921 ዓመተ ምሕረት ዘውድ ጭነው ስለነገሡ ለመታሰብያ የተጻፈ መጽሓፍ" ነው በማለት አበርክተዋል። ከሰማንያ ዓመት በኃላ ደግሞ በድጋሚ ታትሞ ለመውጣት የቻለው በልጅ ልጃቸው በአቶ ሽመልስ ቻሊ ይልማ ብርታትና ጽናት ነው።

ደራሲው የ 'ዋዜማ' ትርጉም በመቅድሙ ላይ በግልጽ አስፍረውታል፦ "ዋዜማ ማለት ከበዓል በፊት የሚውለው ቀን ነው። በዋዜማ ቀን ከካህናቱና ከሊቃውንቱ በቀር ሕዝቡ ሁሉ ወደ ቤተ ክርስትያን አይሰበሰቡም። በበዓሉ ቀን ግን ንጉሡና መኳንንቱ፣ ወታደሩና ባላገሬ፣ ነጋዴውም፣ ሴቶችና ሕጻናት እንኳ ሳይቀሩ በዓሉን ለማክበር ይሰበሰባሉ። በዚሁም በበዓሉ ቀን ካህናቱና ሊቃውንቱ እየዘመሩ ሕዝቡ እልል እያሉ በደስታ ይውላሉ።"

መጽሓፉ ከጥንት ጀምሮ በኢትዮጵያ የነገሡ ነገሥታትና በቅደም ተከተል ዝርዝር ስማቸውና የነገሡበት ዘመን ከማስቀመጡም በላይ፡ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስትያን

በርእሰ ጳጳስነት የመሩት ሊቃውንትም ስማቸውና ያደረጉት አስተዋጽኦ በዝርዝር ተጠቅሷል። ብላቴን ጌታ ኀሩይ ይኽንን መጽሓፍ ከመጻፋቸው በፊት ግን አለቃ ታየ በ1914 ዓ.ም.ኢ. 'የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ' በሚል ርእስ በጻፉት መጽሓፍ ውስጥ ከክርስቶስ ልደት በፊትና ከልደት በኋላ በኢትዮጵያ የነገሡ ነገሥታት፣ የነገሡበት ዘመንና የመንግሥታቸው መጨረሻ በዝርዝር ጽፈውታል። ነገር ግን አለቃ ታየና ብላቴን ጌታ ሳይጠቅሷቸው ያለፉ አንዳንድ ነገሥታት ስላሉ፣ በታሪክ ጥናትና ምርምር የተሰማሩ የአሁኑ ኢትዮጵያውያን ምሁራን አስፈላጊውን መረጃ በማግኘትና በማጣራት የኢትዮጵያን ታሪክ መጻፍ ይኖርባቸዋል።

ለምሳሌ ታዋቂ የነበሩት ሁለት የአክሱም ነገሥታት ማለትም ኢንዲቢስ ና አፊላስ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በመጨረሻው 3ኛ ምእተ ዓመትና በመጀመርያው 4ኛ ምእተ ዓመት የነበሩ ናቸው። በነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁለት መጻሕፍት ውስጥ ስማቸውን አልተጠቀሰም። ኢንዲቢስ አክሱም በገንዘብ ተመን የሚንቀሳቀስ ንግድ እንዲኖራት ያደረገ ነው፣ አፊላስ ደግሞ የተለያዩ ገንዘቦች (የነሓስ፣ የብር፣ የወርቅ) ለሃገርና ለዓለም አቀፍ ንግድ ከመፍጠሩም በላይ የአክሱምን ግዛት ቀይ ባሕርን ተሻግሮ እስከ ሒጃዝ (አሁን ሳውዲ ዓረብያ ውስጥ) ያሰፋ ንጉሥ ነበር። እኚህ ሁለት ታዋቂ ነገሥታት 'መንከባከብና ማስወገድ ያለብን ባህሎች' በሚል ርእስ በደረስኩት መጽሓፍ ውስጥ ጠቅሻቼዋለሁ።

መጀምርያ አለቃ ታየ፣ ተክትለው ብላቴን ጌታ ኀሩይ፣ እኔም ከጻፍኩዋቸው ጽሑፎች በፊት ምሁራን ኢትዮጵያውያን እንደነ ስርግዉ ሃብተሥላሴ፣ ሪቻርድ ፓንከረስት፣ ታደስ ታምራት፣ ባህሩ ዘውዴ፣ ተወልደ ትኩእ ወዘተ በሰፊው ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ጽፈዋል። እንዲሁም በዘልማድ የሚጽፉ ታሪከኞች እንደ ተክለጻዲቅ መኵርያ፣ በላይ ግደይ አምሃ፣ ግርማ ኤልያስ ወዘተ ለኢትዮጵያ ታሪክ ግሩም አስተዋጽኦ አድርገዋል። ነገር ግን የኢትየጵያ ታሪክና ስልጣኔ እጅግ በጣም ሰፊ ከመሆኑም በላይ በርካታ ገጹ ስላልተከሰተና ከፍተኛ ምርምርም ስለሚጠይቅ በመንግስት የተደራጀና በኮሚሽን የሚመራ 'ብሔራዊ የኢትዮጵያ ታሪክና ቅርሳቅርስ ተቋም' ተቋቁሞ የጠፈ ጥናት ማካሄድ ይኖርበታል።

ሰለሆነም፣ ምሁራኑን ለማበረታታትና ተማሪውም በጥናትና ምርምር ፍላጎትና ጉጉት እንድያሳድር ለመንደርደርያ ያህል 'ዋዜማ' ን አቀርብላችኋለሁ።

ብላቴን ጌታ የኢትዮጵያ ነገሥታት ዘመነ መንግሥታት ቅደም ተከተል ከ2545 ከክርስቶስ ልደት በፊት ሲጀምሩት፣ አለቃ ታየ ግን ከልደት በፊት 1985 ዓ.ም. ነው የሚጀምሩት። ይኸም የሆነበት ምክንያት ብላቴን ጌታ በኢትዮጵያ የነገሱ የነገደ ካም ወይም ኩሽ (አሁን ሰሜን ሱዳን) ነገሥታት ብለው ከጅምሩ ስላከሉበት ነው። ሁለቱ ጸሓፊዎች የተስማሙበት ነገር ቢኖር ግን የአግአዝያን ቅደም ተከተል ዘመነ መንግሥት ነው። በሁለቱ መጻሕፍት ማለትም በ 'ኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክና' በ 'ዋዜማ' የመጀመርያው የአግአዝያን ንጉሥ እህናሁስ ሳባ ሁለተኛ ሲሆን፣ በዚሁ ስርወ መንግሥት 52ኛዋ ንግሥት ደግሞ ንግሥተ ሳባ ናት። ከክርስቶስ ልደት በፊት መጨረሻ የነገሰው ባዚን ሲሆን በብላቴን ጌታ ዘመነ ንግሥና አቆጣጠር 139ኛ ሲሆን፣ በአለቃ ታየ ግን 119ኛ ነው። ሁለቱ ደራስያን ግን ባዚን ከልደት በፊት 9 ዓመት፣ ከልደት በኋላ 8 ዓመት፣ በጠቅላላ 17 መንገሡን ይስማማሉ።

ሰፋ ያለና ጥልቀት ያለው ጥናትና ምርምር ያስፈልጋል ያልኩበት አንዱ ምክንያት የዓመተ ምሕረትና የዘመን ቅድመ ሁኔታ ያለመጣጣም (አንዳንዴም መራራቅ) ስለሚኖርና እውነተኛውን ታሪክ በእርግጥ ማስቀመጡ አስቸጋሪ ስለሚሆን ነው።

ሌላ ጥናትና ምርምር የሚያስፈልገው ነገር ቢኖር (ከዚህ ቀደም በሌላ ጽሑፌ ያቀረብኩት) የኢትዮጵያ ጥንታዊ ስልጣኔ ከደቡብ ዓረብ ይልቅ ከግብጽና ከኑብያ በብዙ ረገድ የተቆራኘ ለመሆኑ ነው። የድንጋይና የውቅር ህንጻዎችና ሃዎልቶች፣ ተመሳሳይ የእርሻ ስልት፣ ባህላዊ የእጽና ማዕድን (ጠበል) ሕክምና፣ ተመሳሳይ አውደ አዋርሕ፣ እንዲሁም አንድ ዓይነት የነገሥታት ስሞች በሁለቱ አገሮች ለመግዛታቸው ነው።

በ ዋዜማ ከቀረቡት ነገሥታት፡ አራተኛው ንጉሥ ለምሳሌ ስሙ አሜን ነው፣ ከነገደ አግአዝያን 8ኛው ንጉሥ ስሙ ሔርሐቶር ነው፣ ከምኒሊክ 1ኛ ቀጥሎ የነገሰው 4ኛ ንጉስ ደግሞ አመንሆተፕ ይባላል። ‘አመን’ በጥንታዊት ግብጽ (ከመት) ቋንቋ ‘ሕቡእ’ (የማይታይ) አምላክ ወይም ባጭሩ ‘አምላክ’ ማለት ነው፣ ሐቶር የጥንታዊት ግብጽ (ከመት) አንዷ እንስት አምላክ ነበረች፣ አመንሆተፕ አንድ የግብጽ ፈርዖን ሆኖ የስሙ ቀጥታ ትርጉሙ ደግሞ ‘የሰላም አምላክ’ ማለት ነው። ስለሆነም ኢትዮጵያና ግብጽ በብዙ ረገድ የተሳሰሩ ጥንታዊ ሥልጣኔዎች ነበሩ ማለት ይቻላል።

የጥንት የኢትዮጵያ ነገሥታት ስም በአለቃ ታየና በብላቴን ጌታ እንደተጠቆሙ ከሆነ ስማቸውን አስመልክቶ ቅድመ-ግእዝ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። ስለሆነም የሥነ-ቋንቋ ጥናትና ምርምር የኢትዮጵያን ጥንታዊ ታሪክ በይበልጥ ሊከስትልንና ሊያበለጽግልን ይችላል። ነገር ግን የነገሥታቱ ስም ከመላጎደል ቅድመ-ግእዝ ይሁን እንጂ አንድ ከምኒሊክ 1ኛ በኋላ የነገሰው 9ኛ ንጉስ ግን የትግርኛ ስም ነበረው። ስሙ ደግሞ አኽሱማይ ወረደ ፀሓይ ነው፣ ክክርስቶስ ልደት በፊት ከ 778 ዓ.ም. እስከ 755 ዓ.ም. ለ23 ዓመታት ነግሿል (ዋዜማ ገጽ 33)።

ክርስቶስ ከተወለደ በኋላ፡ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው፡ ባዚን ለ9 ዓመታት ነግሿል፣ ስሙ ከ ‘ባዛ’ ጋር የሚመሳሰል ነው፣ ባዛ የኩናማ ብሔረሰብ ሁለተኛ ስም መሆኑ ነው፣ በጉራጌ ብሔረሰብም ባዛ የሚባል የመናፍስት አምላክ እንደነበር በጥናትና ምርምር አግኝተነዋል።

ከባዚን በኋላ በቅደም ተከተል የነገሡት ሁለት ነገሥታት ሠርጡ ጽንፈ አሰግድ እና አካጥታህ (ጽንፈ አርእድ) ናቸው (ዋዜማ 36)፣ ስማቸው ያለጥርጥር ከቅድመ-ግእዝ ወደ ዘመነ ግእዝ ሽግግርን ያንጸባርቃል። ከነዚሁ ነገሥታት 15ኛው ድድሜ ዘርዓይ ሲሆን፣ 34ኛው ጽጋብ ነው፡ ያለጥርጥርም የትግርኛ ስም ሆኖ ትርጉሙም ‘ጥጋብ’ ነው፣ 40ኛው ንጉሥ ሳሕል ነው፣ 41ኛው አርፍድ (ገብረመስቀል)፣ 42ኛው አድኃና፣ 50ኛው ስሑል፣ 57ኛው ጽባሕ (መሐረነ ክርስቶስ)፣ 71ኛው ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ሳሕል ናቸው፣ ስማቸውም በግልጽ ከግእዝ ወደ ትግርኛ ሽግግርን ያመለክታሉ።

ደራሲው የጥንት የኢትዮጵያ ነገሥታት በዝርዝር ካስቀመጡ በኋላ፣ ከአክሱም ዘመነ መንግሥት በኋላ ስለ ዛጔ ዘመነ መንግሥት ጽፈዋል። የመጀመርያው የዛጔ ንጉሥ መራ ተክለ ኃይማኖት ነው። ስመ መንግስቱ ደግሞ ዛጔ ነው። የዛጔ ትርጉም ለመግለጽ ጸሃፊው በዚህ መልክ ያስቀምጡታል፦

"…በአንዳንድ ታሪክ ውስጥ መራ ተክለ ሃይማኖት የድልንዓድን ልጅ መሶበ ወርቅ የምትባለውን አግብቶ ሸፈተ። ድልንዓድም ሠራዊት ሰብስቦ ቢገጥመው ድል ሆነና ሸሸ። መራ ተክለ ሃይማኖትም መንግሥቱን ወሰደ። ስለዚህም ዛጔ ተባለ። ዛጔ ማለት ዘአጕየየ ማለት ነው። ትርጓሜውም ድልንዓድን ድል አድርጎ እንዲሸሽ ያደረገ ማለት ነው እያለ ተጽፎ ይገኛል። (ዋዜማ 49-50)

ዘ አጕየየ ቃል በቃሉ በትግርኛ 'ኣሯሯጠ' ማለት ነው። በተጨማሪ በመጽሓፌ በ 'መንከባከብና ማስወገድ ያለብን ባህሎች' 'ዛጔ' ከ ' ዑና እንዳ አቦይ ዛጔ' (አክሱም) የፈለቀ መሆኑን ለማስረዳት መኾርያለሁ። የዛጔ ስርወ መንግሥትም የአክሱም ስልጣኔ ተቀጥያ መሆኑን የሚያጠራጥር አይሆንም። በላስታ አከባቢ የቀጠለው የኢትዮጵያ ስልጣኔ በተለይም የስነ-ህንጻና ስነ-ጥበብ ስልጣኔ አክሱማዊ ለመሆኑ ብዙ የታሪክ ተማራማሪዎች የተስማሙበት ጉዳይ ነው። በዛጔ ዘመነ መንግሥት የተሰሩ ከአለት የተፈለፈሉ የውቅር ቤተ ክርስትያኖች የሚከተሉት ናቸው፦

1. ቤተ ደናግል
2. ቤተ ማርያም
3. ቤተ መድኃኔ ዓለም
4. ቤተ መስቀል
5. ቤተ ጎልጎታ
6. ቤተ ቅዱስ ሚካኤል
7. ቤተ ገብርኤል
8. ቤተ አባ ሊባኖስ
9. ቤተ መርቆርዮስ
10. ቤተ አማኑኤል
11. ቤተ ጊዮርጊስ (ዋዜማ 52)

ከዛጔ ዘመነ መንግሥት በኋላ ጸሐፊው የቀዳማዊ ሚኒሊክ ወደ ሆነው ወደ ይኩኖአምላክ (የክርስትና ስሙ ተስፋ እየሱስ) ስርወ መንግሥቱ መተላለፉን ከገለጹ በኋላ ዝርዝር የነገሥታት ስም እስከ አጼ ኃይለ ሥላሴ በቅደም ተከተል አስቀምጠውታል። የሽግግሩም መንግሥት ስልጣን በሚረከብበት ጊዜ ኃይልን በመጠቀም ወይም ደምን በማፍሰስ ሳይሆን በአቡነ ተክለሃይማኖት አማካኝነት በተደረገው የሰላም ድርድር ይትባረክ (የመጨረሻው የዛጔ ንጉሥ) እና ይኩኖአምላክ ባደረጉት ስምምነት ነው። የስምምነቱ አንዱ ነጥብ ይትባረክ ባቀረበው ሐሳብ "ይኩኖአምላክ መንግሥቱን ከተቀበለ በኋላ ከዛጔ ዘር አንድ መስፍን እየመረጠ በላስታ አልጋ እንዲያስቀምጥ፣ የላስታም ግዛት ለዛጔ ወገኖች እንደ ርስት ሆኖ እንዲኖር ነው።" (ዋዜማ 58)

ከይኩኖአምላክ እስከ ሚናስ (የዚሁ ስርወ መንግስት 26ኛው ንጉሥ) ከመሃል አገር ሁኖው ኢትዮጵያን ገዝተዋል። ከነዚሁ ነገሥታት አንዱ አዋቂና ተመራማሪ 19ኛው ንጉሥ አጼ ዘርአያቆብ (ከአክሱም ፈላስፋው ዘርአያቆብ እንዳይምታታ) ነው። እንድያውም ታሪክ በሰነድ መልክ ማስፈርና 'ክብረነገሥት' ን የጀመረው እሱ ነው ይባላል። ለሃገር ነጻነት በአርበኝነትና በጀግነንነት የተዋጉት ደግሞ አጼ ልብነ ድንግልና ልጃቸው አጼ ገላውዴዎስ ናቸው። አጼ ገላውዴዎስ በሃገር ወዳድነቱ ብቻ ሳይሆን በጽሑፎቹም ሳይቀር ታዋቂነት አትርፎ ነበር። ከጻፋቸውም አንዱ መጸሓፍ 'የእምነት ኑዛዜ' የሚል ርእስ ያዘለ ነው።

ከአጼ ሚናስ በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት መናገሻ ወደ ጎንደር ስለተዛወረ ከመጀመርያው ንጉሥ ሠርፀ ድንግል እስከ የመጨረሻው ንጉሥ ተክለጊዮርጊስ 18 ነገሥታት ነግሷል። "ከነዚህም ከ18ቱ ነገሥታት ውስጥ" ይላሉ ብላቴን ጌታ "ስማቸው እጅግ የታወቀና ታሪካቸው የበዛው የሠርፀ ድንግል፣ የሱስንዮስ፣ የፋሲል፣ የኢያሱ አድያም ሰገድ የነዚሁ የአራቱ ነው።" (ዋዜማ 65)

ከመጫረሻው የጎንደር ንጉሥ በኋላ ልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ክፍላተ ሃገራት በመሳፍንቱ መገዛት ስለጀመሩ፣ ንጉሦቹ ወይ በመሳፍንቱ ሥር ለስሙ ገዝተዋል ወይም ደግሞ በእስር (ወህኒ) ጊዜያቸውን አሳልፈውታል። ነገሥታቱ ግን የአንድነት ምልክት መሆናቸውን ታምኖበት ከሥልጣን ቢገለሉም ቅሉ የሞት ቅጣት አይደርስባቸውም ነበር።

በ 'ዋዜማ' እንደተመለከተው ሁሉ 19 መሳፍንት ትግራይ፣ ቤጌምድር፣ ጎጃምና ሸዋን በተናጠል ገዝተዋል። ነገር ግን በመጽሐፉ እንደተገለጸው የመጀመርያው መስፍን ማለትም ትግራይን ያስተዳደሩ ራስ ወልደሥላሴ ሳይሆኑ ራስ ሚካኤል ስሑል ናቸው፣ ስማቸው በ 'ዋዜማ' ባይጠቀስም ሚካኤል ስሑል ትግራይና ምድረ ባሕሪ (አሁን ኤርትራ) እስከ ጎንደር ድረስ ለአርባ ዓመታት ያህል ገዝቷል።

ኢትዮጵያ በመሳፍንት አገዛዝ ለሰባ ዓመታት ያህል ተከፋፍላ ከቆየች በኋላ በቋረኛው ካሣ ወይም አጼ ቴዎድሮስ እንደገና የምትዋሀድበት መንገድ ተፈጠረ። አጼ ቴዎድሮስ ለ15 ዓመት ከገዙ በኋላ ከእንግሊዞች ባደረጉት ጦርነት ሳይሳካላቸው ስለቀረ በ1860 ዓ.ም. ራሳቸውን መስዋእት ስላደረጉ ለሦስት ዓመታት ያህል በአጼ ተክለጊዮርጊስ ተተኩ። በ 1871 ዓ.ም. ግን አባ በዝብዝ ካሣ ወይም አጼ የሓንስ 4ኛ አጼ ተክለጊዮርጊስን አቸንፈው ኢትዮጵያን በይበልጥ በማዋሃድና በማስፋት ለ18 ዓመታት ገዝተዋል።

ብለቴን ጌታ ኅሩይ ስለ አጼ ዮሓንስ ያላቸውን አድናቆት በዚህ መልክ ያስቀምጡታል፦

"አጼ የሐንስ ስመ ጥሩ ጀግና በመሆናቸው ላይ መሓላ አክባሪ እግዚአብሔርን ፈሪ ነበሩ። ስለ ኢትዮጵያም ትልቅ ቅንዓት ነበራቸው። በዘመናቸውም ሁለት ትልልቅ ስራ ሰርተዋል።

1ኛው ትልቅ ስራ። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከተባልሁ በበታቼ ነገሥታትን ማንገሥ ይገባኛል ብለው በሸዋ ንጉሥ ምኒሊክን። በጎጃም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን አንግሠዋል።
2ኛው ትልቅ ሥራ። ሀገሬ ኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብዋም ብዙ ስለሆነ አንድ ሊቀ ጳጳስ እየዞረ ለማስተማርና ለመስበክ አይችልም ብለው ከእስክንድርያ አራት ጳጳሳት አስመጥተዋል።

ነገር ግን እውነተኛውን ትምህርት ያልተማሩ አንዳንድ ካህናት ባጠገባቸው ከማኖራቸው የተነሳ የነዚያን ምክር እየተከተሉ እስላሞችን ሌሎችንም በሃይማኖት ያልመሰሏቸውን ሰዎች ትምባሆም የሚጠጥቱም ሰዎች በአካላቸውና በርስታቸው በገንዘባቸውም ስለ ቀጧቸው የውጭ አገር ጸሓፊዎች ታሪካቸውን አበላሽተው ጽፈውባቸዋል።

ቢሆንም በሀገራቸው ድንበር ላይ ደማቸውን አፍስሰው ስለ ሞቱ ኢትዮጵያን በሚወዱ ሰዎች ዘንድ ስማቸው ለዘላለም አይረሳም።" (ዋዜማ 73)

*መጽሐፉ፡ የኢትዮጵያ ነገሥታት የንግሥና ቅደም ተከተል በዳግማዊ አጼ ሚኒሊክ፡ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ* (በኋላ አጼ ኃይለ ሥላሴ) *ያጠቃልላል።*

ሁለተኛውና ሦስተኛው የመጽሐፉ ክፍሎች ማለትም ከምዕራፍ 12 ጀምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያንን የመሩት ርእሰ ሊቀነ ጳጳሳት ስምና ቁጥር ነው። አራተኛው ክፍል ደግሞ ስለ እጨጌዎች ነው። ስለነዚህ የኃይማኖት መሪዎች ገድል ዝርዝር ሳልገባ አግባቢነት ያላቸውና ለውይይት መንደርደርያ ያህል ጠቃሚ የምላቸውን ነጥቦች ላይ ብቻ ማትኮሩ በይበልጥ ጠቀሜታ አለው ብየ አምናለሁኝ።

ሞራልና ግብረገብነትን አስመልክቶ አሁን ሕብረተሰባችን በትልቅ ውጥረት ስለሚገኝ፡ ኃይማኖት ደግሞ የሞራልና የግብረገብነት መሰረትና መልህቅ ስለሆነ፡ የሕብረተሰቡ አባላት ከኃይማኖት በራቁ ቍጥር ሕብረተሰቡ ይበከላል፣ ፍርክስኩሱም ሊወጣ ይችላል። ይህ እንዳይሆን ታድያ የጻድቃናቱ ገድልና አርአያ መከተል ይኖርብናል።

"ነገር ግን ቅዱሳን ምንም ቢቀያየሙ ደግሞ" ይላሉ ብላቴን ጌታ "ስለ እግዚአብሔር ብለው ይቅርታ ማድረጋቸው አይቀርምና ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ ታሥሮ ሳለ ማርቆስን አምጣልኝ ብሎ ወደ ጢሜቴዎስ ስለጻፈ ጢሜቴዎስ ወስዶ አስታርቆታል። በእሥርም ቤት ሲያገለግለው ነበር 2፡ ጢሞ፡ 4፡11" (ዋዜማ 92)

ይኸንን ከላይ የጠቀስኩትን ግብረገብ-አዘል የይቅርታና እርቅ ቢሂል ደራሲው ቀደም ብለውም አስመልክተዉት ነበር። እንዲህም ይላሉ "ለምሳሌ፡ በሀገራችን በኢትዮጵያ አንድ የታሠረ ሰው በታየ ጊዜ የሚያየው ሰው ሁሉ አሣሪውም እንኳ ሳይቀር እግዚአብሔር ያውጣህ ይለዋል። ይኸውም የኢትዮጵያ ሰዎች በችግርና በመከራ ለሚኖር ሰው ርኅሩኃን መሆናቸውን ያስረዳሉ" (ዋዜማ 55)

ብላቴን ጌታ በሂወት ተመልሰው አሁን ሕብረተሰባችንን ቢያዩትና ቢመረምሩት ግን ወይ ግራ ይጋባሉ ወይም ደግሞ እጅግ በጣም ያዝናሉ። ምክንያቱም ባሁኑ ጊዜ የይቅርታና ምሕረት ግብረገባዊ እምነት በኢትዮጵያችን ያከተመ ይመስላል፣ መልካም ባህሉ እንደገና ካላንሰራራ በስተቀረ።

ሌላው ባሁኑ ጊዜ ሕብረተሰባችን የጎደለው ነገር ቢኖር መቻቻል አለመኖሩና ተቃዋሚ ወይም ተቀናቃኝ ሀሳቦችን አለመቀበልን ነው። በዙዎቻችን የዘነጋነው ነገር ቢኖር ግን የጥንቱ ሕብረተሰባችን በመቻቻል ባህል እጅግ የበለጸገ መኖሩን ነው። ይኸንን ሓቅ አስመልክቶ ከዚህ ቀደም በተለያዩ ጽሑፎቼ አስፍሬዋለሁ፣ በዚሁ አቃቂር ግን በ’ዋዜማ’ የተጠቀሱትን ምሳሌዎች ማቅረብ እሻለሁ፦ 1) የሮማው ርእሰ ሊቀነ ጳጳሳት ልዮን “በክርስቶስ ሁለት ባሕርያት ሳይደባለቁና ሳይቀላቀሉ መኖራቸውን የሚያስረዳ ደብዳቤ ጽፎ…ወደ ኬልቄዶን ልኮ ነበርና የልዮን ደብዳቤ በተነበበ ጊዜ ዲዮስቆሮስ ሁለት ባሕርይ ማለትን አልቀበልም አለ” (ገጽ 76)፣ 2) “አርዮስ የተባለ አንድ የግብጽ ቄስ ወልድ በመለኮቱ ፍጡር ነው የሚል የኑፋቄ ቃል ስለተናገረ ሊቃውንቱ ሁሉ ጉባኤ አድርገው እንዲከራከሩት ጳጳሳት በገላትያ ከተማ በኒቅያ ጉባኤ አደረጉ። የእስክንድርያውም ሊቀ ጳጳሳት እለእስክንድሮስ አፈ ጉባኤ ነበረና ከአርዮስ ጋራ ተከራክሮ ከረታውና ካወገዘው በኋላ ወደ እስክንድርያ ተመልሶ በ321 ዓ.ም. አረፈ” (ገጽ 111)።

በጣም ደስ የሚያሰኝ ነገር ቢኖር የጥንት የኢትዮጵያ ሊቃውንት የሐሳብን ልዩነቶች ለመፍታት በጥላቻና በምቀኝነት ሳይሆን በንግግርና በክርክር፡ የኋላ ኋላም በእርቅና ስምምነት ያምኑ ስለነበር ነው። የዚሁ የመከራከር ባህል አይነተኛ ምሳሌ በአጼ ዳዊት ዘመነ መንግሥት (አሁንም ስለ ክርስቶስ ባሕርይ) የተደረገው ንግግርና ክርክር ነው።

“አባ ክርስቶዶሎ 3ኛ በአጼ ዳዊት ዘመን የነበረ ነው። ዳዊት ክርስቶስ በቅብዓት መንፈስ ቅዱስ የባሕርይ አምላክ ሆነ የሚሉትን የቅባቶችን ሃይማኖት ይወድ ነበርና የቅባት ሃይማኖት ወገኖች ሁሉ ተሰብስበው ክርስቶስ በተወሕዶ የባሕርይ አምላክ ሆነ ከሚሉተ ከደብረ ሊባኖስ ወገኖች አከራክረን ብለው ለመኑት።

አጼ ዳዊትም ወገኖቹን ቅባቶችን ደስ ለማሰኘት ሲል ሊቃውንቱ ሁሉ እንዲሰበሰቡና እንዲከራከሩ ፈቃድ አደረገ። ከዚህም በኋላ በጎጃምና በቤገምድር፣ በአምሐራም የሚኖሩ ሊቃውንቶች ሁሉ ተሰበሰቡ። ከነዚህም እኩሌቶቹ ክርስቶስ በተዋህዶ የባሕርይ አምላክ ሆነ። በቅብአተ መንፈስ ቅዱስ ግን የጸጋ ልጅ ሆነ የሚሉ ነበሩ። እነዚህም ቤተ ተክለ ሃይማኖት ይባላሉ። ዋና ስፍራቸውም ከእጨጌው ጋር በአዘዞ ነበር።

እኩሌቶቹ ደግሞ ክርስቶስ በቅብአተ መንፈስ ቅዱስ የባሕርይ አምላክ ሆነ። በተዋህዶ ግን ሁለትነትን አጥፍቶ አንድ ሆነ የሚሉ ነበሩ። እነዚህም ቤተ ኤዎስጣቴዎስ ይባላሉ። ዋና ስፍራቸውም በጎጃምና ጎንደር ውስጥ በቁስቋም ደብር ነው።

አጼ ዳዊትም ምንም እርሱ የቅባቶችን ሃይማኖት ቢወድ ሊቃውንቱ የተሰበሰቡበት የሃይማኖት ነገር ስለ ሆነ ወደ ጳጳሱ ወደ አባ ክርስቶዶሉ ሔዳችሁ ተነጋገሩ ብሎ ሰደዳቸው።" (ዋዜማ 127)

ሌላ ተመሳሳይ ክርክር የተደረገበት ዓብይ የሃይማኖት ነጥብ የክርሰቶስ ልደት ሮቡዕ ወይም ዓርብ ቢውል ስጋ ይበላል ወይስ አይበላም የሚለወን ጥያቄ ነው። ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል፡ የአጼ አምደ ጽዮን ልጅ አጼ ሰይፈ አርእድ "ያንዳንድ ሊቃውንት ቃል ሰምቶ በዓለ ልደትን በታሕሣሥ 28 ና በ29 ሁለት ቀን አክብሩ። እነዚህም ሁለት በዓላት ረቡዕና አርብም ቢውሉ ማለዳ እየቀደሳችሁ ሥጋ እንድትበሉ ብሎ አዘዘ። ጳጳሱ አባ ያዕቆብና እጨጌ ፊሊጶስ ግን ጌታችን ሁለት ቀን አልተወለደምና በዓለ ልደትን ሁለት ቀን አናከብርም። በታሕሣሥ 28ም ሮብና አርብ ቢውልም ማለዳም አንቀድስም፡ ሥጋም አንበላም ብለው እምቢ አሉ።" (ዋዜማ 149)

በዓለ ልደት ሮቡዕና ዓርብ ከዋለ ሥጋ ይበላል የሚሉ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ግን አሉ። ለምሳሌ በአጼ የሓንስ 1ኛ ዘመነ መንግሥት በአቡን የሚመሩ የአርመን የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ወደ ኢትዮጵያ በመጡ ጊዜ በቤተ መንግስቱ ከነበረው አንዱ ሊቅ ኢትዮጵያዊ ቆስጠንጢኖስ ከቀረበላቸው አንዱ ጥያቄ "ልደት ወይም ጥምቀት ሮቡዕ ወይም ዓርብ ከዋለ ሥጋ ትበላላችሁ ወይ" የሚል ነበር። የአርመኑ አቡንም "አንጾምም፡ እንበላለን" ብለው መለሱ። ቆስጠንጢኖስም የአርመንና የኢትዮጵያ አንድ መሆኑን ስላረጋገጠ ደስ ብሎታል። (የሪቻርድ ፓንክረስት አርታኦት በ The Ethiopian Royal Chronicles, pp. 104-105 ተመልከት)።

ከፍ ብለው የተጠቀሱትን ሃይማኖት-አዘል መልካም ባህሎች በሃገራችን በኢትዮጵያ እንደገና የሚያንሰራሩበት ሁኔታ ለመፍጠር ታሪካችንን በቅጡ ማወቅ ስለሚኖርብን የጠፈ የጥናትና ምርምር እንቅስቃሴዎች ማካሄድ አለብን። የዚሁ እንቅስቃሴ አንዱ አካል የንባብ ባህል ማበረታታትና ማሳደግ ነው፣ ለዚህም ብየ ነው የ 'ዋዜማ' አቃቂር የጻፍኩትና ኢትዮጵያውያን በያሉበት መጽሓፉን እንድያነቡት በትሕትና ሓሳብ አቀርባለሁ።

All Rights Reserved. Copyright Institute of Development and Education for Africa (IDEA), Inc. 2009. Dr. Ghelawdewos Araia can be contacted for educational and constructive feedback via dr.garaia@africanidea.org and the book ዋዜማ can be obtained by contacting Mr. Shimelis Chali Yilma @ 310-293-7377